

# ለኪራይ የሚውል ተሽከርካሪ

**ማስታወቂያ #005**
**ታክሲ/ተደራሽ የታርጋ ሰሌዳ ፈቃድ እድሳት**

**ሜይ 2023**

---

የታክሲ ታርጋ ሰሌዳ ፈቃዶች (T.P.L) እና የተደራሽ ታክሲ ታርጋ ሰሌዳ ፈቃዶች (A.T.P.L) የእድሳት ጊዜ ከ ጁን 1 እስከ ጁን 30 2023 ነው።

ወደዚህ ስራ የሚበዛበት ጊዜ ውስጥ እንደገባን እንደመሆኑ መጠን ለኪራይ የሚውል ተሽከርካሪ ቢሮን ለማግኘት የሚቆዩበት ጊዜ ከመደበኛው በላይ ሊሆን ይችላል፣ ስለዚህም ትዕግስትዎን እና ትብብርዎን እንሻለን። የእድሳት ሂደቱን ኦንላይን ማድረግ ያለውን አዋጭነት እያጣራን ነው፣ ነገር ግን አሁን ለኪራይ የሚውል ተሽከርካሪ እድሳት መከናወን ያለበት በአካል ቢሮ በመምጣት ነው።

ለኪራይ የሚውል ተሽከርካሪ ቢሮ (2340 – 22 ጎዳና NE) ለፈቃድ እድሳቶች ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8:00 am እስከ 4:30 pm ባሉት ሰዓታት ክፍት ነው። የታርጋ ያዢዎች የአልበርታ ስቴት መንጃ ፍቃድዎን ወይም የሚሰራ የታክሲ መንጃ ፍቃድ ይዘው እንዲመጡ እናሳስባለን። ለታክሲ የታርጋ ሰሌዳ ፈቃድ(T.P.L) የእድሳት ክፍያ $495 ነው።

የሊቨሪ የትራንስፖርት መተዳደሪያ ደንብ T.P.Lን ወይም A.T.P.Lን የማደስ አስፈላጊነትን በሚመለከት ድንጋጌዎች አሉት።

> *ክፍል 35*
>
> (1) *T.P.L* ወይም *A.T.P.L* ጊዜው ካለፈ እና ፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜው ባለቀ **በ 30 ቀናት ውስጥ የእድሳት ማመልከቻ ካልቀረበ፣** *T.P.L* ወይም *A.T.P.L* እንደተተወ ተቆጥሮ የመታደስ መብቱ ይሰረዛል።

እርስዎን ጁን ውስጥ ለማየት በጉጉት እጠብቃለሁ። እባክዎን ማንኛውንም ጥያቄ ካልዎት ወደ VFHlicensing@calgary.ca ኢሜይል ያድርጉት

ይህ ማሳወቂያ ወደ አማርኛ፣ አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ህንድኛ፣ ፑንጃቢ፣ ሶማሊኛ እና ኡርዱ ተተርጉሟል። ሰነዶቹን ለማየት እዚህ ጠቅ ያድርጉ።

ከሰላምታ ጋር፣

ዳውን አንስወርዝ
መሪ፣ ለኪራይ የሚውል ተሽከርካሪ ፈቃድ
EMCS፣ የህዝብ ተሽከርካሪ ደረጃዎች